# እርዳታ ካስፈለግዎ

**ለህይወት አስጊ ድንገተኛ ችግር በ 000 መደወል**

ቤትዎ በጣም ከተጎዳ እና እርዳታ ካስፈለግዎ፣ ለ SES በቁጥር **132 500** መደወል።

በተቻለ ፍጥነት የSES ፈቃደኛ ሰራተኞች ይመጣሉ። የእርዳታ ቅድሚያ ስላለው እባክዎ ይታገሱ።

# መጠራረግ

- በቤትዎ ዙሪያ ያለውን መጥረግ መጀመር - የተበታተኑትን ነገሮች ማለት እንደ ቅርንጫፎችና ቆሻሻዎችን ሰብስቦ በማሰር ከውሀ ቆጣሪ፣ ከጋዝ ቆጣሪና ከተለፎን መስመሮች ላይ ማራቅ።
- ስለ ቅጠላቅጠል ቆሻሻና ሌሎች ነገሮችን እንደ የአስቤስቶስ አጥርን ለማስወገድ ለአካባቢ መንግሥት በመደወል ምክር ማግኘት።

# የአስተዳደር ግዛት ድንገተኛ ችግር አገልግሎት

በምእራባዊ አውስትራሊያ ላለ ማህበረሰብ የማእበል ችግርና ሌላ የተፈጥሮ ድንገተኛ ችግር ሲፈጠር በ FESA State Emergency Service (SES) ፈቃደኞች በኩል እርዳታ ያገኛሉ።

SES ፈቃደኞች ለማህበረሰብ የሚረዱት:

- በቤትና በንግድ ሥራ ላይ ለተበላሸ ጊዚያዊ ጥገና በማካሄድ ይረዳሉ። ቋሚ ዘለቄታ ያለው ጥገና ማቀናጀቱ የራስዎ ሀላፊነት ይሆናል። የርስዎን ኢንሹራንስ ኩባንያ ያነጋግሩ።
- የወደቁ ዛፎችን መጥረግ
- በውጥረት ላይ ወይም የተጎዱ ሰዎችን ማዳን
- ለጎርፍ አስጊ በሆነ አካባቢ የአሸዋ ከረጢት ማስቀመጥ
- ሰዎች ቦታ ሲቀይሩ መርዳት

በማእበል ወቅት በቂ ዝግጅት በተደረገበት አካባቢ እንደዚህ አይነቱ እርዳታ በአብዛኛው መጠነኛ ሲሆን ታዲያ ለዚህ ነው በቤቶችና በህይወት ላይ ስለሚከሰት ችግር ለመቀነስ የ SES ፈቃደኞች ለማህበረሰቡ በትጋት የሚያስተምሩት። እነዚህ መስዋእት ከፋይ ቡድኖች በድንገተኛ ችግር ጊዜ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች እርዳታ ለመስጠት በሚያጠፉት ጊዜ፣ በብርድና በነፋስ ለሚጋለጡት ዋጋ ገንዘብ አይከፈላቸውም።

በሀይለኛ ማእበል ጊዜ ብዙ የድንገተኛ ችግር ጥሪ ሊኖር ስለሚችል ታዲያ ጥሪዎች እንደ ሁኔታው ቅድሚያ በመስጠት በተቻለ ፍጥነት SES ፈቃደኞች ይሄዳሉ።

## በድንገተኛ ጊዜ ለማነጋገር የስልክ ቁጥሮች

| | |
|---|---|
| ፖሊስ፣ እሳት፣ አምቡላንስ (ለህይወት አስጊ የሆነ ደንገተኛ ችግር) | 000 |
| በአስተዳደር ግዛት የድንገተኛ ችግር አገልግሎት(SES) እርዳታ | 132 500 |
| ለምእራባዊ የኤሌትሪክ ሀይል | 131 351 |
| ሆሪዞን የኤሌትሪክ ሀይል/Horizon Power | 132 351 |
| ለውሀ ማህበር/Water Corporation | 131 375 |
| ለአሊንታ/Alinta ጋዝ ድንገተኛ ችግርና ብልሽት | 131 352 |

## በበለጠ መረጃ ስለማግኘት

| | |
|---|---|
| FESA ድረገጽ | www.fesa.gov.au |
| BoM ማእበል ማስጠንቀቂያ የምክር መስመር | 1300 659 213 |
| ስለአየር ሁኔታና ማእበል መተበይ | www.bom.gov.au |
| ስለ መንገድ ሁኔታ (በምእራባዊ አውስትራሊያ ዋና መንገዶች) | 138 138 |


Chin, Dinka, Farsi, Vietnamese, Mandarin, Arabic, Indonesian, Somali, Swahili, French, Cantonese, Amharic, Nuer, Karen, Dari, Kirundi, Sudanese Arabic ቋንቋዎች ምክርና በበለጠ መረጃ በ FESA ድረገጽ ላይ ይቀርባል። በጣሊያን፣ ክሮሺያን፣ ቬትናሚስ፣ ኢንዶነሺያ፣ ጀርመን፣ ፖሊሽ፣ ማሰዶኒያ እና ፖርቹጊስ ቋንቋዎች ምክርና በበለጠ መረጃ በ **FESA** ድረገጽ: **www.fesa.wa.gov.au** ላይ ማየት።

*በዚህ ጥራዝ ወረቀት ላይ ያለው መረጃ እንደ ህዝባዊ አገልግሎት እዲጠቅም በ Fire and Emergency Services Authority (FESA) በኩል በፈቃደኝነት የቀረበ ነው። ይህ ጥራዝ ወረቀት ሲዘጋጅ ከጥሩ እምነትና ከታመኑ ምንጮች የተወሰደ ስለነበር በሚታተምበት ጊዜ ትክክለኛ እንደነበር ነው። ይሁን እንጂ ስለመረጃው ታማኝነትና ትክክለኛነት ዋስትና መስጠት አይቻልም እንዲሁም መረጃውን በመጠቀም ወይም ባለመጠቀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚከሰት ማንኛውም ሀላፊነት የFESA እንደማይጠየቅ የክህደት ቃሉን ይገልጻል። ይህ ጥራዝ ወረቀት እንደ መንደርደሪያ ሊጠቅም ተብሎ የወጣ ስለሆነ አንባቢዎች ተጽእኖ የሌለበት የራሳቸውን ምክር እና ለራሳቸው ጠቃሚ ጥያቄዎች ማግኘት አለባቸው።*

*ሚያዚያ/April 2010*

FESA
FESA House, 480 Hay Street Perth, Western Australia 6000
GPO Box P1174, PERTH WA 6844
**ተለፎን**: +61 8 9323 9300 **ፋክስ**: +61 8 9323 9384
**ኢሜል**: fesa@fesa.wa.gov.au
**ድረገጽ**: www.fesa.wa.gov.au

Amharic



# ለአውሎ ነፋስና ሀይለኛ ዝናብ ዝግጅት ማድረግ





Government of **Western Australia**
**Fire & Emergency Services Authority**

FESA

## የሀይለኛ ዝናብና አውሎ ነፋስ ወቅት

በየዓመቱ ከግንቦት እስከ ጥቅምት ባለው መካከል አውሎ ነፋስ (ማእበል) በደቡባዊ ግማሽ ምእራባዊ አውስትራሊያ ላይ ከባድ ዝናብ፣ አደገኛ ነፋስ፣ መብረቅ፣ ማእበል፣ ጎርፍና ሀይለኛ ነፋስ ሊያመጣ ይችላል። ይሁን እንጂ ማእበል በሞቃት ወራትም ሊከሰት ስለሚችል ታዲያ ዓመቱን በሞላ ዝግጅት በማድረግ መጠበቁ አስፈላጊ ነው።

## የአውሎ ነፋስ ማእበል ማለት ምንድ ነው?

ከምድር አጠገብ ያለ ሙቀት፣ ውሀ አዘል አየር በፍጥነት ወደ ላይ ያልተረጋጋ ህዋን ሲገፋ የአውሎ ነፋስ ማእበል ይፈጠራል።

## ለምንድ ነው ለማእበል ዝግጅት የሚደረግ?

አደገኛ ነፋስ፣ ፍሳሽ ጎርፍ፣ መብረቅ፣ ማእበልና ሀይለኛ ነፋስ በቤቶች፣ መኪናዎችና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከስት ይችላል። በህይወት ላይ ጉዳት ወይም ሞትን ሊአስከትሉ ይችላሉ።

በቤት ላይ ጉዳት ስለሚያመጣ ማእበል መንስሄው:

- ከጣራ የተሰራበት እቃዎች መላላትና መሰበር
- ከወደቁ ዛፎችና ቅርንጫፎች
- ከህንጻ አሸንዳና ቱቦ መዘጋት በሚከሰት ጎርፍ

ሰዎች ዝግጅት በማድረግ በቤታቸው ለሚከሰት ጉዳት መቀነስና ያለ ችግር መኖር ይችላሉ።

## እንዴት መዘጋጀት እንደሚቻል

ቤተሰብዎንና ቤትዎን ለማእበል ማዘጋጀት የራስዎ ሀላፊነት ነው። ማእበል በሚከሰትበት አካባቢ የሚኖሩ ከሆነ ከመጋቢት እስከ ግንቦት ባለው ጊዜ ቀደም ብለው በቤትዎ ውስጥና ደጁ ላይ ያለን ዝግጅት ማጠናቀቅ አለብዎ። ጉዳትን ለመቀነስ ሊረዳ የሚችል አንዳንድ ቀላል እርምጃዎች አሉ:

- የቤትዎ ጣራና አሸንዳዎች ስለመጎዳታቸው ወይም የተላቀቀ ነገር ካለ ማየት
- በአሸንዳዎችና ቱቦዎች ላይ ቅጠሎትና የዘጉት ማጽዳት
- በቤትዎ አካባቢ ያሉትን ቅርንጫፎች መቁረጥና በኤሌትሪክ መስመር ላይ ያለን ዛፍ ለማስወገድ ተቋራጮችን መቅጠር።
- በቅጥር ጊቢ፣ በረንዳ ወይም ጣሪያ የሌለው መናፈሻ ላይ ያሉትን ቆሻሻ ማስወገድ እና የተሰበሩ እቃዎችን ማስወገድ
- ለድንገተኛ ችግር የሚሆን መያዣ ይህም ራዲዮ፣ ላንባዲና፣ መቀየሪያ ባትሪዎች፣ የመጀመሪያ እርዳታ መያዣ እና በድንገተኛ ችግር ለቤተሰብ የወጣ እቅድ
- ቤተሰብዎ ማእበልና ስለሚያስከትለው ችግር ማወቃቸውን ማረጋገጥ
- ለድንገተኛ ችግር እቅድ ማዘጋጀት ይህም ምናልባት ቤትዎ በጎርፍ ከተጥለቀለቀ ስለሚሄዱበት ቦታ እቅድን ያካትታል። ለቤት እንስሳት ምን ማድረግ እንዳለብዎ ግምት ውስጥ ማስገባትና እንዴት የጋዝ፣ ኤሌትሪክና ውሀ መግልገያዎችን መዝጋት እንዳለብዎ ማወቅ (ለበለጠ መረጃ የFESA ድረገጽን ማየት)
- ለድንገተኛ ችግር የስልክ ቁጥሮችን ዝርዝር መለጠፍ
- ለቤትና ለእቃዎች በቂ ዋስትና ኢንሹራንስ ስለመኖሩ ያረጋግጡ

## ስለ አየር ሁኔታ ማስጠንቀቂያ

ስለ ማእበል የሚሰጠው ማስጠንቀቂያና ምክር በየጊዜ መያዝ ይችላሉ:

- በራዲዮ የዜና አውታር፣ በተለቪዥን ወይም በመስመር ላይ አማካኝነት የሚተላለፈውን
- በ FESA ድረገጽ www.fesa.wa.gov.au
- በአየር መቆጣጠሪያ ቢሮ ድረገጽ: **www.bom.gov.au** - ወይም በእነሱ መሬት አየር ሁኔታ ማስጠንቀቂያ እና በጎርፍ ማስጠንቀቂያ ምክር መስጫ መስመር በቁጥር **1300 659 213** መደወል


## ማእበል ስለመምጣቱ ግምት ሲነገር

- በቤትዎ ወይም በሥራዎ አካባቢ ያለን ቆሻሻ ማስወገድና የላላ እቃ ካለ ማስወገድ ወይም ደህንነቱን ማስጠበቅ ምክንያቱም በማእበል ጊዜ ሀይለኛ ነፋስ የተላቀቁ እቃዎችን ወደ መግደል የሚችል ተወንጫፊ ሚሳይል ሊቀይራቸው ይችላል።
- የተላቀቁ እቃዎች በሀይለኛ ነፋስ ሊንሳፈፉ ስለሚችሉ ታዲያ አሸዋ በሞላ ፕላስቲክ ከረጢት መጫን
- ለድንገተኛ ችግር ያዘጋጁት እቃ ወቅታዊ ስለመሆኑ ማረጋገጥ
- የርስዎ የቤት እንስሳትና ውሻና ድመንት በደህና ቦታ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ
- መኪናዎትን ከመጠለያው ማውጣት
- ከቤትዎ እርቀው ከሄዱና የቤትዎ ደህንነት ስለመጠበቁ ለማረጋገጥ ከቤተሰብዎ ወይም ጓደኛዎት ጋር ግንኙነት ማድረግ አለብዎ።
- የቦታው ህንጻ ሠራተኞች ማንኛውንም የላላ የህንጻ እቃዎችን በማስወገድና ለራሳቸው ደህንነቱ የተጠበቀ መጠለያ ያስቀምጣሉ።
- ጀልባዎች በሚገባ መታሰራቸውን የጀልባ ባለንብረቶች ማረጋገጥ አለባቸው።
- ለካምፕ ነዋሪዎች ሌላ አማራጭ መጠለያ ማግኘት አለባቸው።

ለህጻናት፣ በእድሜ አዛውንት ለሆኑና ለአካለ ጉዳተኛ የሆኑ የቤተሰብ አባላት ለየት ያለ ምግብና መድሀኒት ሊያስፈልጋቸው ይችል ይሆናል።

### ለድንገተኛ ችግር የተዘጋጀ እቃ



## በማእበል ጊዜ

- መጋረጃዎችን ዘግተው ከመስኮት ራቅ ብሎ በቤትዎ ውስጥ መቆየት
- ማእበሉ ከውጭ ከተያያዘ ከዛፎች፣ የኤሌትሪክ መስመሮች፣ ከብረት እቃዎች፣ ከውሀ ማጠራቀሚያ መውረጃ፣ ከወንዞችና ምንጮች ራቅ ያለና ደህንነቱ የተጠበቀ መጠለያ ቦታ መፈለግ ነው
- ጀልባ የሚቀዝፉ፣ የሚዋኙ ወይም በውሀ ላይ የሚያንሳፍፉ ከሆነ ትቶ መሄድ
- መብረቅ ካለ የኤሌትሪክ ሶኬትን ማውጣትና የቤት ተለፎንን አለመጠቀም
- ጎርፍ ካለ የፕላስቲክ ከረጢት ወይም የትራስ ጨርቅ ተጠቅሞ አሸዋ በመሙላት የራስም የአሸዋ ከረጢት መፍጠር ይቻላል
- በሀይለኛ ዝናብ ውስጥ የሚነዱ ከሆነ በመንገዱ ላይ ተጨማሪ ጥንቃቂ መውሰድ:
  - ቀስ ማለት፣ መብራቶችን ማብራት እና ከሌሎች ሹፌሮች ጋር ያለን እርቀት ደህና ስለመሆኑ መጠበቅ
  - ማየት ካልቻሉ መኪናዎን ማቆምና ዝናቡ እስኪቆም ድረስ የአደጋ ምልክት መብራቱን አብርቶ መኪና ማቆም
  - ጥልቀቱ ባልታወቀ ውሀ ፍሰት ላይ አለመንዳት

## ከማእበል በኋላ

- በቤትዎና ንብረት ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ማየት
- ጓደኞችና ጎረቤታሞች እርዳታ ካስፈለጋቸው መጠየቅ
- ከጎርፍ ፍሳሽ፣ ወንዞች፣ ምንጮችና የውሀ መፍሰሻዎች ላይ ህጻናትን ማራቅ
- የወደቀ ኤሌትሪክ መስመር አደገኛ ስለሆነ መራቅ
- ከወደቀ ዛፎችንና ከተጎዳ ህንጻዎች ጥንቃቄ ማድረግ
- ቀስ ብሎ ሲነዱ ከሌላ ሹፌሮች ያለው እርቀት ደህንነቱን መጠበቅና ጎርፍ ባለበት አካባቢ ጥንቃቄ መውሰድ
- በመንገድ ላይ ጎርፍ ካለ ጥልቀቱ ባልታወቀ ውሀ ፍሰት ላይ አለመንዳት
- የኮረኮንች መንገድ የሚያዳልጥና ጭቃማ በመሆኑ ለተሽከርካሪዎች ረግረግ ስለሆነ ማስወገድ